የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር 5-0/94/10
Ref. No
ቀን 25 ነሐሴ 2010
Date

በአባሪው ለተዘረዘሩት

በያሉበት

ጉዳዩ:- የድህረ ዕቃ አወጣጥ አጠቃላይ ኦዲት መምረጫ ማኑዋል ይመለከታል፤

የድህረ ዕቃ አወጣጥ የመስክ ኦዲት መረጣን ስጋትን መሰረት ባደረገ መልኩ እንዲከናወን ለማድረግ የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የሥጋት መምረጫ ማንዋል ተዘጋጅቶ በስጋት ስራ አመራር ኮሚቴው በኩል ውይይት ተደርጎበት ፀድቆ ወደ ሥራ እንዲገባ ተደርጓል።

በዚሁ መሠረት ከ2011 ዓ.ም በጀት ጀምሮ የድህረ ዕቃ አወጣጥ የአጠቃላይ (Comprehensive) ኦዲት መረጣው በሥጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት አማካኝነት በማዕከል እየተመረጠ በኦዲት ዕቅዱ መሰረት ለየቅ/ጽ/ቤቶቹ የሚላክ መሆኑን እየገለፅኩ ማንዋሉን እና የፀደቀበትን ቃለ-ጉባኤ 19 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር ተይይዞ መላኩን አስታውቃለሁ።

ከሰላምታ ጋር

በመዶ ቶሬሶ
የጉምሩክ ሥራዎች ዘርፍ
ም/ዋና ዳይሬክተር

ግልባጭ:

- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለጉምሩክ ሥራዎች ዘርፍ
- ለስጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስጣን



ስልክ ቁ / Tel.. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ -ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

ለ አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ለ አዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

አዲስ አበባ፣

ለ ሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ለ ሐዋሳ ገቢ.ዎችና እና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ለ ባህር ዳር ገቢ.ዎች እና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ለ ኮምቦልቻ ገቢ.ዎች እና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ለ መቀሌ ገቢ.ዎች እና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ለ አዳማ ገቢ.ዎች እና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ለ ድሬዳዋ ገቢ.ዎች እና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ለ ጅማ ገቢ.ዎችና እና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ለ ሚሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ለ ሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ለ ጅጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ለ ጋላፊ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ለ ኦዲት አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ለ አገር ውስጥ ታክስ አሰራርና ድጋር ዳይሬክቶሬት

ለ ጉምሩክ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ለ ዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክተር

ለ ኢንተለጀንስ ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ለ መረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

ለ ደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ለ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

**በያሉበት**

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

በህግ ማስከበር ዘርፍ

የስጋት ስራ አመራር ኮሚቴ

ስጋትን መሠረት ያደረገ የድህረ-ዕቃ አወጣጥ የመስክ ኦዲት የመምረጫ መስፈርት የአሠራር

ማኑዋል ላይ የተደረገ ውይይት እና የውሳኔ ሃሳብ

ቃለ-ጉባዔ

የስብሰባው ቦታ፡ - በዋና መ/ቤት በህግ ማስከበር ዘርፍ የስብሰባ አዳራሽ

የስብሰባው ቀን፡ - ሐምሌ 24 ቀን 2010 ዓ.ም.

የስብሰባው ሰዓት፡ - ከጠዋቱ 3:00 - 6:40 (ሰዓት)

በስብሰባው ላይ የተገኙ፡ -

1. አቶ ዘመዴ ተፈራ ................ የህግ ማስከበር ዘርፍ ም/ዋ/ዳይሬክተር ሰብሳቢ
2. አቶ ከበደ ልደቱ ................ የስጋት ስራ አመራር ዳይሬክተር አባል
3. አቶ አዘዘው ጫኔ ................ የአ/አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ሥ/አስኪያጅ አባል
4. አቶ አዲስ አየለ ................ የሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ አባል
5. አቶ ዘርዑ ገብሩ ................ የኦዲት አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክተር አባል
6. ወ/ሮ አባይነሽ አባተ ............ የአገር ውስጥ ታክስ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክተር አባል
7. አቶ ገ/ኅይወት ገ/ስላሴ .......... የአ/አ/ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ አባል
8. አቶ ኃይም ይብራህ .............. የጉምሩክ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክተር አባል
9. አቶ ወንድወሰን ደገፋ ............ የዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክተር ተወካይ
10. አቶ ሲሳይ ገዙ ................ የኢንተለጀንስ ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክተር አባል
11. አቶ ብርሃኑ ማሞ ................ የመረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር ዳይሬክተር አባል
12. አቶ ዮሴፍ ሽፈራው .............. የደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክተር አባል

በስብሰባው ላይ ያልተገኙ፡ -

ወ/ሮ ሂሩት መብራቴ ...................... የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ*/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ አባል

ሌሎች በስብሰባው ላይ የተገኙ፡ -

ወ/ሮ ብርቱካን ግርማ ...................... የቀድሞ የድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክተር

## 1. የስብሰባው አጀንዳ

የድህረ ዕቃ አወጣጥ የመስክ ኦዲት የመምረጫ መሥፈርት የአሠራር ማኑዋል ላይ ውይይት ማድረግና ማጽደቅ

### 1.1. የተነሱ ዋና ዋና ሃሳቦች

የድህረ ዕቃ አወጣጥ የአጠቃላይ ኦዲት መረጣ ስጋትን መሰረት ባደረገ አኳኋን መምረጥ ተገቢ መሆኑን በማመን እንደ ተቋም በህግ ማስከበር ዘርፍ በተሰጠ አቅጣጫ አዲሱ አደረጃጀት ተገባራዊ ከሆነበት ጊዜ አንስቶ ሥጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት የመረጣ ስራወን ለማከናወን የተለያዩተግባራትን ሲከውን ቆይቷል፡፡ በዚህም መሰረት የመምረጫ መስፈረቶችን እና ዝርዝር አሰራሩን በተመለከተ የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ በማየት የዳታ ማቺንግን አሰራር እና እሳቤ ተግባራዊ በማድረግ፣ በጉምሩክ በኩል የነበረንን ልምዶችና አሠራሮች እንዲሁም በአገር ውስጥ ታክስ ላይ ያለውንም ልምድ በመጠቀም የድህረ ዕቃ አወጣጥ የአጠቃላይ ኦዲት መረጣ ስጋትን መሰረት ባደረገ አኳኋን እንዴት ትንታኔውን እንሥራ በማለት ጥናት ተደርጐ ማኑዋሉ ተዘጋጅቷል፡፡ የተዘጋጀውም ማኑዋል ለኮሚቴው እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

በስብሰባውም በስጋት ስራ አመራር የተዘጋጀውን ሰነድ አስመልክቶ ለስጋት ስራ አመራር ኮሚቴው በማቅረብ የተለያ ሃሰብ እና አስተያየቶች ከኮሚቴው አባላት ተነስተው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡ የስጋት ስራ አመራር ኮሚቴውም በተዘጋጀው ማኑዋል ላይ በመሰረታዊነት በመወያየት ስምምነት ላይ ተደርሷል፣ ይህ አሰራር የጉምሩክ አሠራርን ለማሻሻል ዋነኛ መሣሪያ በመሆኑ ጊዜንና ገንዘብን በሁለቱም ወገን የሚቀንስ /በአስመጪውና በጉምሩክ/ መሆኑን በመግለጽ ለ2011 መረጣውን በዋናው መ/ቤት አጠቃላይ ኦዲት /Comprensive Audit/ ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ለየብቻ መምረጣቸው ስለማያስኬድ በተቀመጡት ስምንት መስፈርቶች መሠረት ከወዲሁ እየተሰራ ያለውን ሂደት አጠናቅሮ በመቀጠል መረጣውን አጠናቆ በኦዲት እቅዱ መሰረት ለቅ/ጽ/ቤቶች ከኦዲት ዳ/ሬቱ እና ከዘርፉ ጋር በጋራ በመሆን መከናወን እንዳለበት አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ እንዲሁም በተነሱ ሃሰብ እና አስተያየቶች ዙሪያ ውይይት እና ማብራሪያ በመስጠት የሚካተቱ ዝርዝር ሃሳቦችን በሰነዱ እንዲካተቱ ሰነዱ የስራ ማኑዋል ሆኖ ሥራ ላይ እንዲውል ውሳኔ ሚያስፈልጋቸው ጉዳዮችን አተኩሮ በመወያየት ውሳኔ አሳልፏል፡፡

## 1.2. የተወሰኑ እና አቅጣጫ የተሰጠባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች

በወይይቱ ወቅት በድህረ ዕቃ አወጣጥ የመስክ ኦዲት መምረጫ መሥፈርቶች ላይ ይውጣ፣ ይከፈል፣ ይቀጥል፣ የሚለው ላይ አንድ በአንድ ውይይት በማድረግ፣ የሚከተሉት ውሳኔዎች ተላልፈዋል፡፡

1.2.1. የቀረቡት የመምረጫ መስፈርቶች በቀረበው መሰረት የሚያሰሩ መሆናቸውን አድባብድ በመመልከት ተግባራዊ እንዲሆኑ ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

1.2.2. ለእያንዳንዱ መምረጫ መሥፈርት የተሰጠው ክብደቱ ከእነምክንያቱ በመግለጽ እና ለተነሱት ጥያቄዎች መልስ እና ማብራሪያ በመስጠት የመሥፈርቶቹ ክብደት ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ ተብለው በቅደም ተከተል እንደሚከተለው እንዲሆን ተወስኗል፡፡

| ተ.ቀ. | የመምረጫ መሥፈርት | የተሰጠ ክብደት | ክብደት መቶኛ |
|---|---|---|---|
| 1 | የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ጠቅላላ መጠን | 3 | 17.65 |
| 2 | በጉምሩክ ያላቸው ፕሮፋይል | 3 | 17.65 |
| 3 | በአገር ውስጥ በኩል ያላቸው የሥጋት ደረጃ | 3 | 17.65 |
| 4 | የሚጠቀሙት የጉምሩክ አስተላላፊ | 2 | 11.76 |
| 5 | የድርጅቱ የኋላ የጥፋተኝነት ታሪክ | 2 | 11.76 |
| 6 | የዕቃዎች የሥሪት ሀገር | 2 | 11.76 |
| 7 | የኢንቨስትመንት ዘርፍና የንግድ ሥራ መስክ | 1 | 5.88 |
| 8 | የዕቃዎች ጭነት ሀገር | 1 | 5.88 |
| | ድምር | 17 | |

1.2.3. የመጨረሻ የስጋት ደረጃ መወሰኛ ጣሪያ/Threshold/ በተመለከተ የሚመጣውን ውጤት በስጋት ስራ አመራር በሚያሰቀምጠው መሰረት ከፍተኛ፣መካከለኛ፣ዝቅተኛ የሚወሰን ይሆናል፡፡

1.2.4. ማኑዋሉ ከሦስቱ የኦዲት አይነቶች ለአጠቃላይ ኦዲት ብቻ የሚሠራ መሆኑን በማፀደቅ ለሌሎቹ የኦዲት አይነቶች ወደፊት በዕቅድ በጋራ የሚታይ መሆኑን በመውሰድ ይህን ይዞ ወደስራ ቶሎ መለወጥ የሚገባ መሆኑ ተገልጿል፡፡

1.2.5. የቀረበው ሠነድ  ዝርዝር ጉዳዮችን የያዘ ስለሆነ ማኑዋል እንዲባል

1.2.6. ከትርጉም እስከ ወሰን የተሰጡ ግብዓቶች እንዲካተቱ

1.2.7. 1.7 እና 2.2 አንድ ስለሆኑ በአንድ ቢጠቃለሉ ለተባለው አስተያየቶች አንድ ቢመስሉም የየራሳቸው አገላለጽ ስላላቸው ባሉበት እንዲቀጥሉ

1.2.8. ለሌሎች የኦዲት አይነቶችን መምረጫ መስፈርት እስኪዘጋጅ ቀድሞ ሲሠራበት የነበረውን መርህ ተከተለው ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲሰሩ

1.2.9. ከሀገር ውስጥ ታክስ ኦዲት አሰራር ጋር ባማቀናጀት የመምራቱን ስራ የኦዲት ዳ/ሬቱ በዕቅድ የሚመለስ እንዲሆን

በመጨረሻም አሁን ያለውን ተቀብለን በሂደት የሚገጥሙ ችግሮችን በጋራ እየፈቱ ወደፊት መሄድ እንደሚገባ በመግባባት ስብሰባው 6:40 ተጠናቋል፡፡

# በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

## የሥጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት

## የድህረ ዕቃ አወጣጥ የአጠቃላይ ኦዲት የመምረጫ መስፈርት

## የአሰራር ማኑዋል

ነሀሴ 2010

አዲስ አበባ

## ማውጫ


ምዕራፍ አንድ ....................................................................................................................3

1.1. መግቢያ ....................................................................................................................3

1.2. ትርጉም ....................................................................................................................4

1.3. የማኑዋሉ ዓላማ ..........................................................................................................6

1.4. የድህረ-ዕቃ አወጣጥ አጠቃላይ ኦዲት መረጣ አሰራር ማኑዋል አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ........6

1.5. የማኑዋሉ ወሰን ..........................................................................................................7

1.6. የድህረ ዕቃ አወጣጥ የመስክ ኦዲት ትኩረት መስኮች ......................................................7

ምዕራፍ ሁለት ....................................................................................................................9

የድህረ ዕቃ አወጣት የመስክ ኦዲት መረጣ አሰራር ..................................................................9

2.1. ለኦዲት መረጣው ጥቅም ላይ የሚውሉ የመረጃ አይነቶችና የመረጃ ምንጮች ........................9

2.2. ሥጋትን መሰረት ያደረገ የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የሚያተኩርባቸው ድርጅቶች/ሰዎች .............9

2.3. የድህረ ዕቃ አወጣጥ የአጠቃላይ ኦዲት መምረጫ መስፈርት እና ዝርዝር አሰራር .................10

2.4. ለአጠቃላይ ኦዲት መምረጫ መስፈርቶች የተሰጠ ክብደት ...................................................15

2.5. የስጋት ትንታኔ የመጨረሻ አተገባበርን በተመለከተ ........................................................15

2.5.1. የመምረጫ መስፈርቶቹ ትንታኔ በተመለከተ ...............................................................15

2.5.2. አጠቃላይ የመጨረሻ የመምረጣ ትንታኔን በተመለከተ ....................................................16

2.6. ክትትልና ግምገማ /Monitor and Review/ ..................................................................17

ማጠቃለያ ........................................................................................................................19

## 1.1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዘመናዊ የጉምሩክ አስተዳደር ለማዘመን እና ለመገንባት ዘርፈ ብዙ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል፡፡ ከነዚህ ተግባራት ውስጥ የጉምሩክ አሰራርን በስጋት ስራ አመራር እንዲሁም የድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲትን መሰረት ባደረገ አሠራር ሥርዓት እንዲመራ በማድረግ የተቀላጠፈ አገልግሎትን እና የተመጣጠነ ቁጥጥር እንዲኖር ማስቻል ነው፡፡ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ የንግድ እንቅስቃሴ እየተስፋፋ በመምጣቱ ምክንያት የተፋጠነና የተቀላጠፈ አገልግሎት አሰጣጥ መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም ዕቃን ከጉምሩክ ክልል ቁጥጥር ለማውጣት የሚያስፈልገውን ጊዜና ገንዘብ ከመቀነሱም በላይ የነጋዴውን ትርፋማነት የሚጨመር ይሆናል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ግብር ከፋዮች ታማኝነታቸውን ለማረጋገጥ እና የቁጥጥር ስርዓቱ አገልግሎት አሰጣጠጡን በማይጎዳ መልኩ ለማከናወን ስጋትን መሰረት ያደረገ የድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የአሠራር ስርዓት ወሳኝ ነው፡፡

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 121 ንዑስ አንቀፅ 1 የድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት አጠናቀዉ የተለቀቁ ዕቃዎችን ዲክላራሲዮን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ዕቃዉን ለማስመጣት ወይም ወደ ዉጭ አገር ለመላክ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በተሳተፈ ሰዉ እጅ የሚገኙ መዛግብትን፣ ሪከርዶችን፣ የንግድ አሠራሮችን እና ሌሎች አግባብነት ያላቸዉን ጉምሩክ ነክ የንግድ መረጃዎችን በመመርመር የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ሊያደርግ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም የድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ፅንሰ ሃሳብም ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ተፈጽሞባቸው በተቀለጠፈ ሁኔታ ከተለቀቁ በኂላ በስጋት ደረጃቸው መሠረት ውጤታማ ቁጥጥር ማድረግ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት የህግ ተገዢነት የሚረጋግጥበት ሂደት ነው፡፡

ይሁን እንጂ ለዚህ ተግባር የሚያግዝ ዘመናዊ እና በመረጃ ቴክኖሎጂ የታገዘ የአሰራር ስርዓት ባለመኖሩ እስካሁን ባለው ሂደት በተበታተነ መልኩ ወጥ የሆነ አሰራር ሳይኖረው ቆይቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ለኦዲት መረጣው የሚያግዝ በዘመናዊ መረጃ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሠራር ስርዓት ባይኖርም ድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ማንዋል፣WCO GUIDE LINE VOL- 2ን እንዲሁም የስጋት ስራ አመራር መርህን መሰረት ባደረገ መልኩ በቀጣይ ስርዓቱ ተፈጥሮ ተግባራዊ እስኪደረግ የድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት በዚህ የአሰራር ማኑዋል ላይ የተገለፁትን መምረጫ መስፈርቶች

Ethiopian Revenues and Customs Authority

ይሆናል።

ማኑዋሉም ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን በክፍል አንድ ትርጉም፣ ዓላማ፣ አስፈላጊነት፣ ጠቀሜታ እና የድህረ ዕቃ አወጣጥ የትኩረት አቅጣጫዎችን የያዘ ሲሆን በክፍል ሁለት የድህረ ዕቃ አወጣጥ አጠቃላይ ኦዲት መረጣ ዝርዝር የአሰራር ይዟል።

## 1.2. ትርጉም

1) **"የስጋት ስራ አመራር" ማለት፡-** በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 2 ቁጥር 45 መሰረት የስጋት ስራ አመራር ማለት ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገቡ/በገቡ፣ በሚወጡና በሚተላለፉ ዕቃዎች ላይ አገልግሎት አሰጣጡንና የቁጥጥር ሥርዓቱን ሚዛናዊ ባደረገ ሁኔታ በሚቀመጡ መስፈርቶች መሠረት የተለያየ የስጋት ደረጃ በማውጣት የሚከናወን የአሰራር ሥርዓት ነው።
2) **ድህር ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ማለት፡-** ዕቃዎች ከጉምሩክ ክልል ውጭ ከተለቀቁ በኋል የሚደረግ ቁጥጥር ነው። አዋጅ 859(121)(1)
3) ***የድህረ-ዕቃ አወጣጥ አጠቃላይ ኦዲት /Comprehensive Audit/ ማለት፡-*** በጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም ሂደታቸውን ጨርሰው በገቡ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሂደት ላይ ባሉ ወይም በጊዚያዊነት ዕቃ ያስገቡ ድረጅቶችን በአዋጅ በተቀመጠው ጊዜ ገደብ መሠረት በማድረግ ተገቢው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት በጉምሩክ አዋጅ መሠረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ እና ህግን ለማስከበር የሚከናወን የኦዲት ተግባር ነው።
4) **"ቀይ ስጋት ደረጃ"** ማለት ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ማለት ሲሆን በፍተሻ መመሪያ መሰረት አካላዊ የዕቃዎች ወይም የመንገደኞች ፍተሻ እና የሠነድ ምርመራ እንዲደረግ የሚገልጽ መስመር (channel) ነው።
5) **"ቢጫ ስጋት ደረጃ"** ማለት መካከለኛ የስጋት ደረጃ ማለት ሲሆን ሰነድ ምርመራ እንዲደረግ የሚገልጽ መስመር (channel) ነው።
6) **"አረንጓዴ ስጋት ደረጃ"** ማለት ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ማለት ሲሆን በመድረሻ ጣቢያ የደረሱ ዕቃዎች ወይም መንገደኞች የሰነድና የአካላዊ ፍተሻ ሳይደረግባቸው የገቢ ዕቃ ሰነድ እንደቀረበ ወይም መንገደኛው እንደደረሰ በመልቀቅ በድህረ- ዕቃ አወጣጥ ኦዲት እና በሌሎች ዕቃ ከተለቀቀ በኋላ ቁጥጥር በሚያደርጉ የህግ ማስከበር የስራ ክፍሎች ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚችሉ መሆኑን የሚገልጽ መስመር ነው።

Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 7

የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ድርጅቶች(AEO) የሚስተናገዱበት የስጋት ደረጃ ሲሆን፤ በመድረሻ ጣቢያ የደረሱ ዕቃዎች የሰነድና የአካላዊ ፍተሻ ሳይደረግባቸው የገቢ ዕቃ ሠነድ እንደቀረበ ተለቀው በድህረ- ዕቃ አወጣጥ ኦዲት እና በሌሎች የህግ ማስከበር የስራ ክፍሎች ዕቃው ከተለቀቀ በኋላ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚችሉ መሆኑን የሚገልጽ መስመር ነው።

8) **"የልዩ መብት ተጠቃሚ"** ማለት በተቋሙ በተቀመጠ የአሰራር ሥርአት መሰረት በሚመለከታቸው አካላት ተመርጠው የተቀላጠፈ መስተንግዶ እንዲያገኙ የሚደረጉ ድርጅቶች ናቸው።

9) **"የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች "/AEO/** ማለት በአቅርቦት ሰንሰለት ተሳታፊ የሆኑና በባለሥልጣኑ የተዘጋጁ ዝቅተኛ መስፈርቶችን በማሟላት በተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ፕሮግራም የታቀፉ ሰዎች/ድርጅቶች ማለት ነው።

10) **"የስጋት ስራ አመራር ደረጃ"** ማለት በተደረገ የስጋት ትንታኔ መነሻ ወይም በተቀመጠ የስጋት መስፈርት መሰረት የአንድን ዕቃ፣ ተሽከርካሪ ወይም መንገደኛ የመስተንግዶ መስመር የሚገልጽ ነው።

11) **"የጉምሩክ ዋጋ ዝርዝር መግለጫ** (Valuation Details Declaration [VDD])" :- ማለት ከዕቃ ዲክሌራሲዮን በተጨማሪ የገቢ ዕቃዎችን የጉምሩክ ዋጋ ለመተመን የሚያስፈልጉ መግለጫዎችና መረጃዎችን በዲክላራሲዮን አቅራቢው በመሙላት ለባለስልጣኑ በዝርዝር የሚያሳውቅበት በባለሥልጣኑ የተዘረጋ ሥርዓት ወይም የተዘጋጀ የኤሌክትሮኒክ መረጃ ማሳወቂያ ሥነ-ሥርዓት ሲሆን፤ በወረቀት መልክ የሚዘጋጅ ቅጽንም ይጨምራል።

12) **"የኢትዮጵያ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ሥርዓት** (Ethiopian customs valuation system [ECVS]) ":- ማለት በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ያገኙ የገቢ ወይም ወጪ እቃዎች ዋጋ መረጃን እና የአለማቀፍ ዕቃዎች ዋጋ መረጃን መሠረት በማድረግ የሚደራጅ ለዋጋ ማነጻጸሪያነት የሚያገለግል የመረጃ ዳታቤዝ ነው።

13) "Tax Payear Risk Data Profile (TPRDP)":- የግብር ከፋዮች ከጥፋት ጋር በተያያዘ መረጃ የሚደራጅበት ዳታ ቤዝ ነው።

14) **"ባትሎአድ"** :- ማለት ባህር ትራንዚት ሎጅስቲክ አገልግሎት ድርጅት ነው።

15) **"ቅ/ጽ/ቤት"**:-ማለት የባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ናቸው።

16) **"አዋጅ"** ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ነው።

እና መመሪያ ላይ ያሉትን ትርጉሞች ይይዛሉ።

## 1.3. የማኑዋሉ ዓላማ

በድህረ-ዕቃ አወጣጥ (የመስክ ኦዲት) ኦዲት ሊደረጉ የሚገቡ ድርጅቶችን ስጋት ሥራ አመራር ስርዓትን መሠረት በማድረግ መለየትና እንዲተገበር በማስቻል የኦዲት ውጤታማነትና የህግ ማስከበር ስርዓቱን በማጠናከር የህግ ተገዥነትን ማረጋገጥ ነው።

## 1.4. የድህረ-ዕቃ አወጣጥ አጠቃላይ ኦዲት መረጣ አሰራር ማኑዋል አስፈላጊነትና ጠቀሜታ

በአገራችን ያለው የወጭ እና የገቢ ንግድ እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ ምክንያት ይህንን መሰረት በማደረግ የጉምሩክ አሰራርን በማዘመን እና ቀልጣፋ መስተንግዶ በመስጠት እቃ ከተለቀቀ በኋላ ቁጥጥር ስርዓቱን ማጠናከር ይኖርበታል። በመሆኑም አገሪቱ የምትከተለዉ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ግብርና ቀረጥን የማሳወቅ ዘዴን /Self Assessment/ በመሆኑና በጉምሩክ ዕቃ አወጣጥ ሂደት ላይ በቀልጣፋ የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት የሚስተናገዱ እየጨመሩ በመምጣታቸው የድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ሃላፊነትና ድርሻ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ በመምጣቱና በሥጋት ሥራ አመራር መሠረት በየቅ/ጽ/ቤቱ የመስክ ኦዲት የሚደረጉ ድርጅቶችን በማዕከላዊነት ለመምረጥ ማስቻል ነው።

በመሆኑም እንደ ተቋም ወጥነት ያለው የስጋት ስራ አመራር መርህን መሰረት ያደረገ የድህረ ዕቃ አወጣጥ የመስክ ኦዲት አመራረጥ ሂደት እንዲኖር በማስቻል ዉጤታማ የሆነ የኦዲት ስራ እንዲከናወን በማስፈለጉ ሥጋትን መሰረት ያደረገ የመስክ ኦዲት መረጣ አሰራር አስፈላጊ ይሆናል።

በመሆኑም የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡-

- በቅ/ጽ/ቤቱ በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ ኦዲት የሚደረጉ ድርጅቶችን ዕቅድ ለማዘጋጀት እና የቅጽ/ቤቱን የኦዲት ስምሪት በውጤታማነት መምራት ያስችላል።
- በመንግስት የተሰጡ መብቶችን በመከታታል፣ በመቆጣጠር እና በማረጋገጥ በመብቱ ተጠቃሚዎች የሚገቡ ዕቃዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን በማረጋገጥ ለመንግስት ፖሊሲ አፈጻጸም አካላት ግብዓት ይሰጣል፣ የንግድ ሂደቱን ያሳልጣል፣ ሳይሰበሰብ ይቀር የነበር የመንግስት ቀረጥና ታክስ እንዲሰበሰብ ያደርጋል።

## 1.5. የማኑዋሉ ወሰን

ይህ ማኑዋል የጉምሩክ ሥነ ስርዓት ሙሉ በሙሉ አጠናቅቀዉ(አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሂደት ላይ ባሉ) በጊዚያዊነትም ይሁን በቋሚነት ወደ አገር በገቡ እና ከአገር በወጡ የገቢና ወጪ ዕቃዎች ላይ በጉምሩክ አዋጅ የተቀመጠዉን መሠረት በማድረግ ሥጋትን መሰረት አድረጎ በሚመረጡ እና የመስክ ኦዲት በሚደረጉ ሰነዶች/ድርጅቶች/ሰዎች ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 1.6. የድህረ ዕቃ አወጣጥ የመስክ ኦዲት ትኩረት መስኮች

ከታች የተዘረዘሩት እና በአብዛኛው በእቃ አወጣጥ ወቅት በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ የሚስተናገዱ ድርጅቶች እና በተለያዩ የስራ ዘርፎች ተሰማርተው ከመንግስት የቀረጥ ቅናሽ መብት ተጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶች ማለትም፡-

### ሀ. የጉምሩክ ልዩ መብት ተጠቃሚዎች፣

የልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ህዳር 4 ቀን 2006 ዓ.ም በቁጥር 3.0/396/14 ከጉምሩክ ዘርፍ በተጻፈ ደብዳቤ በተላለፈው የአሰራር ስርአት መሰረት የጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን በሲስተም በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ የሚስተናገዱ እና በድርጅቶቹ ላይ የሚደረገው ቁጥጥር እቃዎች ከተለቀቁ በኂላ በድህረ ዕቃ አወጣጥ ማረጋገጥ የመስተንግዶ ስርዓቱን በትክክል ህግን አክበረው እየሄዱ መሆኑን ማወቅ አስፈላጊ በመሆኑ የድህረዕቃ አወጣት ኦዲት ትኩረት የሚሰጥባቸው ይሆናል፡፡

### ለ. የተመረጡ ኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች (AEO) ፣

መንግስት በሰጠው አቅጣጫ እና ተቋሙ ባስቀመጠው መስፈርት መሰረት የተለያዩ አስመጪዎች እና ላኪዎችን ለማበረታታት በወርቅ፤ በብር እና በነሀስ ደረጃ ወጥቶላቸው በጉምሩክ ስነ ስርዓት በተለየ ቀልጣፋ መስተንግዶ እየተፈጸመላቸው በሰማያዊ መስመር እንድያልፉ ማለትም በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ተመድበው በመድረሻ ጣቢያ የደረሱ ዕቃዎች የሰነድና የአካላዊ ፍተሻ ሳይደረግባቸው የገቢ ዕቃ ሠነድ እንደቀረበ ተለቀው በድህረ- ዕቃ አወጣጥ ኦዲት እና በሌሎች የህግ ማስከበር የስራ ክፍሎች ዕቃው ከተለቀቀ በኂላ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚችሉ በመሆኑ ትኩረት የሚደረግባቸው ይሆናል፡፡

### ሐ. የሁለተኛ መደብ የታሪፍ ቅናሽ ተጠቃሚዎች

የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ ተጠቃሚዎች ከሌሎች አስመጪዎች እና ላኪዎች በተለየየቀረጥ እና ታክስ ቅናሽ የሚያገኙ ሲሆን በመመሪያ ቁጥር 126/2009 አንቀጽ

መርሆችን መሰረት በማድረግ የኦዲት ቁጥጥር የሚደረግባቸውን የጉምሩክ ሁለተኛ መደብ ታሪፍ ቅናሽ ተጠቃሚዎችን እንደሚመርጥ የሚያስቀምጥ በመሆኑ ትኩረት የሚደረግባቸው ይሆናል፡፡

**መ. የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚዎች፣**

በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት የጉምሩክ ስነ ስርዓት አፈጻጸም መመሪያ 86/2005 እንደተደነገገው የሀገራችን ኢንደስትሪ ዕድገት በማፋጠን የኢኮኖሚ ልማትን የማረጋገጥ እና ልማቱ እና ኢንቨስትመንት የሚያስፈለገውን የውጭ ምንዛሬን ግኝቶችን ማጎልበት እንዲያስችል መንግስት የተለያዩ ማበረታቻ ስርዓቶችን እንደ ተመላሽ ቀረጥ ስርዓት፣የቫውቸር ደብተር አሰጣጥ፣የቦንድድ ኤርፖርት ፋብሪካ ስርዓት አሰጣጥ፣የቦንድድ ኤርፖርት ማምረቻ መጋዘን ስርዓት እና የቦንድድ ግባዓት አቅርቦት መጋዘን ስርዓት ለአምራች ላኪዎች፣ለቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች፣ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች እና ላኪዎች ተሰጥቷል፡፡ በመሆኑም እነዚህ መብቶች በትክክል ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው የምናረጋግጥበት መንገድ አንዱ የድህረ ዕቃ አወጣት ኦዲት በሆኑ የትኩረት ቦታዎች ይሆናሉ፡፡

**ሠ. በመንግስት የተሰጡ መብቶችን ተጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶች፣**

በተለያየ ጊዜ በመንግስት ለተለያዩ አላማዎች እና ኢኮኖሚውን ለመደጎም የተለያዩ የቀረጥ ቅናሽ ወይም የቀረጥ ነጻ መብት የሚያሰጡ አሰራሮችን እና መመሪያዎችን ያወጣል በዚህም መሰረት እነዚህ መብቶቹ በትክክል ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው የምናረጋግጥበት አንዱ ዘዴ የድህረ ዕቃ አወጣጥ በመሆኑ የትኩረት አቅጣጫዎቹ ይሆናሉ፡፡

**ረ. በጊዜያዊነት ለፕሮጀክት ዕቃ የሚያስገቡ ድርጅቶች**

በጊዜያዊነት ለፕሮጀክት ዕቃ የሚያስገቡ ድርጅቶች ዕቃዎቹን ሲያስገቡ ምንም አይነት ቀረጥ እና ታክስ የማይከፍሉባቸው በመሆኑ እና እቃዎቹ ተመልሰው ካልወጡ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ከፍተኛ በመሆኑ የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የስጋት አካላት ከሆኑት መካከል ይመደባሉ፡፡

ሸ. ሌሎች በዕቃ አወጣጥ ወቅት በመካከለኛ እና በከፍተኛ ስጋት ደረጃ የሚስተናገዱ ድርጅቶችን ኦዲት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሚደረግ ይሆናል፤

# የድህረ ዕቃ አወጣት የመስክ ኦዲት መረጣ አሰራር

## 2.1. ለኦዲት መረጣው ጥቅም ላይ የሚውሉ የመረጃ አይነቶችና የመረጃ ምንጮች

ሥጋትን መሰረት ያደረገ የኦዲት መረጣው ከተለያዩ ምንጮች የሚሰበሰቡ መረጃዎችን ሲሆን በዋናነት እንደመረጃ ምንጭነት የሚጠቀማቸውም፡-

**ከውስጥ የሚሰበሰቡ መረጃዎች፡-**

- በሲስተም የሚያዙ የሪከርድ መረጃዎች ከጉምሩክ ዳታ ቤዝ(አሲኩዳ፣eCMS)፣ ከስጋት ስራ አመራር ዳታ ቤዝ(TPRDP(ከጉምሩክ የተለያዩ የስራ ክፍሎች ከሚያዙ መረጃዎች (ከፍተሻ፣ ከድንገተኛ ፍተሻ፤ ከኢንተለጀንስ፤ ከድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት፣ ከፓትሮሊንግ እና ኮንትሮባንድ ክትትል ወዘተ)፣ ECVS፣ VDD፣ እና የመሳሰሉት ይሆናሉ።
- ከአገር ውስጥ ታክስ ከሲግታስ፣ከስጋት ስራ አመራር ቡድን፣ከቅ/ጽ/ቤቶች ከተለያ የስራ ክፍሎች፤

**ከውጭ የሚሰበሰቡ መረጃዎች፡-**

- ከሶስተኛ ወገን፤ SINGLE WINDOW(ከተጓዳኝ መ/ቤቶች የሚገኙ መረጃዎች ከባትሎአድ፣ ከኢንዱስትሪ ሚ/ር፣ ከንግድ ሚ/ር፤ ከትራንስፖርት ሚኒስተር፣ ከባንክ እና ከኢንሹራንስ፣ከምርመራ፤ ከአቃቤ ህግ፤ወዘተ) ይሆናል።

## 2.2. ሥጋትን መሰረት ያደረገ የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የሚያተኩርባቸው ድርጅቶች/ሰዎች

ለድህረ ዕቃ አወጣጥ የአጠቃላይ ኦዲት ድርጅቶችን በስጋት ስራ አመራር ለመምረጥ የትኩረት መስክ የሚሆኑት የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ. የጉምሩክ ልዩ መብት ተጠቃሚዎች፣

ለ. የተመረጡ ኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች፣

ሐ. የሁለተኛ መደብ የታሪፍ ቅናሽ ተጠቃሚዎች እና አምራቾች

መ. የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚዎች፣

ተጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶች፣

ረ በጊዜያዊነት ለፕሮጀክት ዕቃ የሚያስገቡ ድርጅቶች

ሸ. እንዲሁም ከላይ ከተዘረዘሩት ውጭ ብዙ ዕቃ በማስመጣት ብዛት ከፍተኛ እንዲሁም የስጋትን ተለዋዋጭ ባህሪን ታሳቢ በማድረግ ሌሎች በስጋት ስራ አመራር በኩል ሲካተቱ ይገባል ተብሎ የታመነባቸውን ተቋማት በዳይሬክቶሬት ደረጃ ተወያቶ ሲታመንበት ሊያካትት ይችላል፡፡

ድርጅቶች ከላይ በተዘረዘሩት የትኩረት አቅጣጫዎች መሰረት ከተለዩ በኋላ ከታች በተዘረዘሩት መስፈርቶች መሰረት በሚሰራ እና በሚወጣ የስጋት ደረጃ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ ተብለው ለኦዲት መረጣ ዝግጁ የሚሆኑ ይሆናል፡፡

## 2.3. የድህረ ዕቃ አወጣጥ የአጠቃላይ ኦዲት መምረጫ መስፈርት እና ዝርዝር አሰራር

ለድህረ ዕቃ አወጣጥ የአጠቃላይ ኦዲት መረጣ ለማከናወን ስምንት የመምረጫ መስፈርቶችን ጥቅም ላይ ለማዋል ታሳቢ የተደረገ ሲሆን መምረጫ መስፈርቶቹ እና የአሰራር ዝርዝራቸው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ የአንድን ድርጅት የስጋት ደረጃ ለመወሰን ከታች የተዘረዘሩት መስፈርቶችን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሊጠቀም ይችላል፡፡

1. **የቀረጥ እና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ጠቅላላ መጠን /የገቢ ወይም ወጭ ንግድ CIF/**

   የህን መስፈርት ጥቅም ላይ ለማዋል የመስፈርቱን አጠቃቀም በተመለከተ ሶስት አማራጮችን የምንከተል ሲሆን፦

   ሀ) ለመረጣ ከተለዩ ድርጅቶች መካከል ከፍተኛ የንግድ እንቅስቃሴ ያለቸውን (መረጃው በተወሰደበት አመት በአጠቃላይ ወደ አገር ከገቡት ወይም ከወጡት እቃዎች 80 በመቶ በላይ የንግደ እንቅስቃሴ የሚሸፍኑትን) በመለየት የተለዩትን አጠቃላይ ዝርዝር አማካይ በማውጣት ከፍተኛ መካከለኛ ዝቅተኛ ለማለት ሚዛናዊ ክፍፍል (Normal distribution curve) በመጠቀም የሚወሰን ይሆናል፣ ወይም

   ለ) ለመረጣ ከተለዩ ድርጅቶች መካከል ከተዘረዘሩት ድርጅቶች ድምር አማካይ ጋር ሲነጻጸር ያለው የድርጅቱ የቀረጥ እና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ጠቅላላ መጠን /የገቢ ወይም ወጭ ንግድ CIF/ ልዩነት ከ7.5 በመቶ በላይ

ወይም

ሐ) ለመረጣ ከተለዩ ድርጅቶች መካከል ከተዘረዘሩት ድርጅቶች ድምር አማካይ ጋር ሲነጻጸር ያለው ልዩነት ከ5 ፐርሰንት በታች ከሆነ ዝቅተኛ፣በ5 ፐርሰንት እና በ7.5 ፐርሰንት መካከል ከሆነ መካከለኛ፣ከ7.5 ፐርሰንት በላይ ከሆነ ከፍተኛ በማለት ሊወሰን ይችላል።

2. **በጉምሩክ ያላቸው ፕሮፋይል፤(ከፍተኛ ፣መካከለኛ ፣ዝቅተኛ)**

የዚህን መስፈርት የስጋት ደረጃ ለመወሰን ሁለት አማረጮችን የምንከተል ሲሆን

ሀ) አንደኛው መንገድ የስጋት ስራ አመራር ፕሮፋይል ማደራጃ ሲስተም (data base) ላይ የሚገኝ መረጃን መሰረት በማድረግ የድርጅቶችን የስጋት ደረጃ ከፍተኛ፣መካከለኛ፣ዝቅተኛ በማለት፤ ወይም

ለ) የእያንዳንዱን ድርጅት ስጋት የመከሰት እድል እና ስጋቱ የሚስከትለውን ተጽዕኖ በመለካት የሁለቱን ጥምርታ የመጨረሻ ወጤት በስጋት ስራ አመራር የመወሰኛ ሰንጠረዥ (matrix) በመወሰን ይሆናል።

3. **በአገር ውስጥ በኩል ያላቸው የስጋት ደረጃ (ከፍተኛ ፣መካከለኛ ፣ዝቅተኛ)**

በአገር ውስጥ በኩል ያላቸውን የስጋት ደረጃ ለመወሰን መረጣው ውስጥ ለምዘና የተካተቱ ድርጅቶች ከአገር ውስጥ ስጋት ትንተና በቀጥታ በመውሰድ ከፍተኛ መካከለኛ ዝቅተኛ ተብሎ የሚካተት ይሆናል።

4. **የሚጠቀሙት የጉምሩክ አስተላላፊ(ከፍተኛ ፣መካከለኛ ፣ዝቅተኛ)**

የዚህን መስፈርት የስጋት ደረጃ ለመወሰን ሶስት አማረጮችን የምንከተል ሲሆን

ሀ) አንደኛው መንገድ የስጋት ስራ አመራር ፕሮፋይል ማደራጃ ሲስተም (data base) ላይ የሚገኝ መረጃን መሰረት በማድረግ የድርጅቶችን የስጋት ደረጃ ከፍተኛ፣መካከለኛ፣ዝቅተኛ በማለት ፤ ወይም

ለ) የእያንዳንዱን ጉምሩክ አስተላላፊ ወይም የኦዲት መረጣው ውስጥ ለምዘና የተካተተው ድርጅት የተጠቀማቸው አስተላላፊዎችን መረጃ በማደራጀት በጥቅል አጠቃላይ ስጋት የመከሰት እድል እና ስጋቱ የሚስከትለውን ተጽዕኖ በመለካት የሁለቱን ጥምርጣ የመጨረሻ ወጤት በስጋት ስራ አመራር የመወሰኛ ሰንጠረዥ (matrix) የመወሰን ይሆናል።

ሐ) ወይም ሶስተኛው መንገድ የእያንዳንዱ የጉምሩክ አስተላላፊ የስጋት ደረጃ ከተወሰነ በኋላ የስጋት ስኮሪንግን መሰረት በማደረግ መረጣው ውስጥ

የስጋት ደረጃ ወደ አንድ ለማምጣት ወደ ቁጥር ደረጃ ውክልና (ስኮሪንግ) በመቀየር የሚዛናዊ ክፍፍል (Normal distribution) በመጠቀም ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ትሬሽሆልድ በመወሰን ዝቅተኛ፣መካከለኛ፣ከፍተኛ ተብሎ የሚወሰን ይሆናል፤

ይህም ሲባል <u>የስጋት ደረጃዎች ሲባዛ (X) በእየ ስጋት ስኮሪንግ</u> x 100

ሲካፈል ለአጠቃላይ የጉምሩክ አስተላላፊዎች ብዛት

ለምሳሌ:- ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ያላቸው የጉምሩክ አስተላላፊዎች ብዛት=4

መካከለኛ የስጋት ደረጃ ያላቸው የጉምሩክ አስተላላፊዎች ብዛት=3

ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ያላቸው የጉምሩክ አስተላላፊዎች ብዛት=3

ለስጋት ደረጃዎቹ የተሰጣቸው የቁጥር ደረጃ ውክልና (ስኮሪንግ)

| | |
|---|---|
| ዝቅተኛ | 0 |
| መካከለኛ | 1 |
| ከፍተኛ | 2 |

በሚዛናዊ ክፍፍል (Normal distribution) ለስጋት ደረጃዎች የተቀመጠ ትሬሽሆልድ

| | |
|---|---|
| ዝቅተኛ | 0…≤0.66 |
| መካከለኛ | 0.66…≤1.33 |
| ከፍተኛ | >1.33…≤2 |

የጉምሩክ አስተላላፊዎች አጠቃላይ የቁጥር ደረጃ ውክልና (ስኮሪንግ)

$= \frac{4*0+3*1+3*2}{10}$ =0.9=የመጨረሻ የስጋት ደረጃ =መካከለኛ

5. **የድርጅቱን የኋላ የኦዲት ታሪክ በዴስክ ኦዲት እና ከውስን ኦዲት ግኝት(audit history)፣ እና የወንጀል ወይም የፍታብሔር፣የኢንተለጀንስ እንዲሁም የኢንቨስቴጌሽን ኦዲት ሪከርድ (offence record) ካለ፤(ከፍተኛ፣ዝቅተኛ)**

የዚህን መስፈርት የስጋት ደረጃ ለመወሰን በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ከዚህ በፊት የተደረጉ ኦዲቶችን መሰረት በማደረግ እንዲሁም የወንጀል ወይም የፍታብሄር፣የኢንተለጀንስ እንዲሁም የኢንቨስቲገሽን ኦዲት ሪከርድ ካለበት ከፍተኛ ደረጃ የሚሰጠው ሲሆን ከሌለበት ደግሞ ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ እንዲሰጠው ይደረጋል።

1) የስራት ሀገር የስጋት ደረጃን ለመወሰን ከታች የተዘረዘሩትን ንዑስ መስፈርቶች የምንከተል ሲሆን

ሀ) ስጋት የመከሰት እና ስጋቱ የሚያሳድረው ተጽዕኖ (likelihood and consequence risk)፡ መሰረት በማደረግ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ በመባል ይወሰናል።

ለ) የአካላዊ ፍተሻ ውጤት (Examination result Risk)፡ መሰረት በማደረግ በስታትስቲካል ዲስትርቡሽን ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ በመባል ይወሰናል።

ሐ) ሀገራት ከዚህ ቀደም ያላቸው ተሞክሮ (Risk Based on knowledge)፡ በመነሳት ከፍተኛ እና ዝቅተኛ በመባል የወሰናል።

መ) የንግድ ስምምነት በተመለከተ፡ ስምምነት ከተደረገባቸው አገራት የሚያስመጡ ከፍተኛ ሲባሉ ሌሎቹ ከነዚህ ሀገራት ያላስመጡት ደግሞ ዝቅተኛ ተብለው ይመደባሉ።

በመጨረሻም የአራቱን ጥምርታ በስጋት ደረጃ ክብደት አሰጣት ወደ ቁጥር በመቀየር የመጨረሻውን ውጤት የአራቱን አማካይ አውጥቶ በስታስቲካል ዲስትሪቢውሽን ወይም በማኑዋል በሚደረግ ውሳኔ ይወሰናል።

2) ከሁለት በላይ ሃገራት በሚሆኑበት ጊዜ ለጉምሩክ አስተላላፊዎች የተከተልነውን ሁለተኛውን አማራጭ ልንከተል እናችላለን። ወይም

3) ሶስተኛው መንገድ የእያንዳንዱ የዕቃዎች የሥሪት አገር የስጋት ደረጃ ከተወሰነ በኋላ የስጋት ስኮሪንግ መሰረት ድርጅቱ የተጠቀማቸውን የዕቃዎች የሥሪት አገር የስጋት ደረጃ ወደ የቁጥር ደረጃ ውክልና (ስኮሪንግ) በመቀየር የሚዛናዊ ክፍፍል (Normal distribution) በመጠቀም ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ትሬሽሆልድ በመወሰን ዝቅተኛ፣መካከለኛ፣ከፍተኛ ተብሎ የሚወሰን ይሆናል፤

ይህም ሲባል <u>የስጋት ደረጃዎች ሲባዛ (X) በእየ ስጋት ስኮሪንግ</u> x 100

ሲካፈል ለአጠቃላይ የጉምሩክ አስተላላፊዎች ብዛት

ለምሳሌ:- ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ያላቸው የዕቃዎች የሥሪት አገር ብዛት=1

መካከለኛ የስጋት ደረጃ ያላቸው የዕቃዎች የሥሪት አገር ብዛት=4

ለስጋት ደረጃዎቹ የተሰጣቸው የቁጥር ደረጃ ውክልና (ስኮሪንግ)

| | |
|---|---|
| ዝቅተኛ | 0 |
| መካከለኛ | 1 |
| ከፍተኛ | 2 |

በሚዛናዊ ክፍፍል (Normal distribution) ለስጋት ደረጃዎች የተቀመጠ ትሬሽሆልድ

| | |
|---|---|
| ዝቅተኛ | 0…≤0.66 |
| መካከለኛ | 0.66…≤1.33 |
| ከፍተኛ | >1.33…≤2 |

የዕቃዎች የሥሪት አገር አጠቃላይ የቁጥር ደረጃ ውክልና (ስኮሪንግ)= $\frac{1*0+4*1+5*2}{10}$ =1.4=የመጨረሻ የስጋት ደረጃ =ከፍተኛ

7. **ዕቃዎች የተጫኑበት አገር (ከፍተኛ፣መካከለኛ ፣ዝቅተኛ)**

   ይህን መስፈርት ለመወሰን ከላይ ለስሪት አገር የተከተልነውን አካሄድ ተከትሎ የሚወሰን ይሆናል።

8. **የኢንቨስትመንት ዘርፍና የንግድ ስራ መስክ (ከፍተኛ፣መካከለኛ፣ዝቅተኛ)**

   በዚህ መስፈርት አጠቃቀም ረገድም መረጃው ውስጥ ለምዘና የተካተተው ድርጅት በአገር ውስጥ ታክስ በኩል በሚገኝ የስጋት መረጃ መሰረት በማደረግ ከፍተኛ፣መካከለኛ እና ዝቅተኛ ተብሎ የሚመደብ ይሆናል።

## 2.4. በአጠቃላይ አዲት መምረጫ መስፈርቶች የተሰጠ ክብደት

በስጋት ስራ አመራር መርህ ሁሉም መምረጫ መስፈርቶች እኩል ክብደት ስለማይኖራቸው የክብደት መለኪያ ማስቀመጥ እና የተጽኖ መጠናቸውን መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ ለተቀመጡት የአጠቃላይ አዲት መምረጫ መስፈርቶች ከታች በሰንጠረዥ በተቀመጠው መልኩ የተሰጣቸውን ክብደት ተቀምጧል።

| ተ.ቁ | መስፈርት | የተሰጠ ክብደት | የክብደት መቶኛ |
|---|---|---|---|
| 1 | የቀረጥ እና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ጠቅላላ መጠን | 3 | 17.65 |
| 2 | በጉምሩክ ያላቸው ፕሮፋይል | 3 | 17.65 |
| 3 | በአገር ውስጥ በኩል ያላቸው የስጋት ደረጃ | 3 | 17.65 |
| 4 | የሚጠቀሙት የጉምሩክ አስተላላፊ | 2 | 11.76 |
| 5 | የድርጅቱን የኋላ የጥፋተኝነት ታሪክ | 2 | 11.76 |
| 6 | የዕቃዎች የሥሪት አገር | 2 | 11.76 |
| 7 | የዕቃዎች የጭነት አገር | 1 | 5.88 |
| 8 | የኢንቨስትመንት ዘርፍና የንግድ ስራ መስክ | 1 | 5.88 |
| ድምር | | 17 | 100 |

## 2.5. የስጋት ትንታኔ የመጨረሻ አተገባበርን በተመለከተ

### 2.5.1. የመምረጫ መስፈርቶቹ ትንታኔ በተመለከተ

የእያንዳንዱ መምረጫ መስፈርት የመመረጫ መስፈርቱ አተገባበርን በተመለከተ መረጃዎች ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ከተሰበሰቡ በኋላ የትንታኔ ስራው በእያንዳንዱ መስፈርት ከላይ በእያንዳንዱ መምረጫ መስፈርት ስር በተዘረዘረው መሰረት የሚከናወን ይሆናል።

የመስፈርቶቹን ትንታኔ ከተከናወነ በኋላ በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት የስጋት ጥምርታ በመስራት የእያንዳዱን መምረጫ መስፈርት በተሰጥው ክበድት እያባዙ በመደመር የሚመጣውን አጠቃላይ ድምር ለተሰጠው ክብደት አጠቃላይ ድምር በማካፈል የሚሰራ ይሆናል። ይህም ሲባል የድርጅቶን የስጋት ደረጃን ለመወሰን የመስፈርቶቹን የመጨረሻ የስጋት አማካይ ማግኘት አስፈላጊ በመሆኑ ከታች በተቀመጠው ቀመር የማጠቃለል ስራ ይሰራል።

$$\text{የድርጅቶቹ የስጋት ደረጃ መወሰኛ አማካይ} = \frac{\text{የእያንዳንዱ መስፈርት የስጋት ደረጃ * የተሰጠው ክብደት አጠቃላይ ድምር}}{\text{የክብደቶቹ አጠቃላይ ድምር}}$$

የሚመጣውን ውጤት በስጋት ስራ አመራር በሚወሰን የስጋት ደረጃ መወሰኛ ጣሪያ/Threshold/ ከፍተኛ፣መካከለኛ፣ዝቅተኛ ከሚባሉት ውስጥ በኦዲት ዕቅድ መሰረት ከከፍተኛው በመነሳት ወደዝቅተኛው በመውረድ ለኦዲት የሚተላለፉ ይሆናል።

ለምሳሌ፡- ከታች በተዘረዘረው ሰንጠረዥ እንደምንመለከተው እያንዳንዱ ድረጅት በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ተመዝኖ ከተሰጠው ክብደት ጋር ተባዝቶ አና ለክብደቶቹ ተካፍሎ በሚገኘው አጠቃላይ ውጤት የመስፈርቶቹ አማካይ መሰረት የድርጅቶቹ ከታች በተቀመጠው መሰረት ቢሆን የድርጅቶቹ የስጋት ደረጃ ከታች በሰንጠረዡ በተዘረዘረው መሰረት ለማሳየት ተሞክሯል።

ለምሳሌ፡- የተቀመጠ የስጋት ደረጃ መወሰኛ ጣሪያ/Threshold/

| |
|---|
| [illegible] |
| ቢጫ >0.66≤0.94 |
| [illegible] |

| Company | CIF | coff | Coustoms Profile | coff | Transitaire | coff | Domestic profile | coff | Froud history | Coff | Origin | Coeff | Consignment | Coeff | Business type | Coeff | Risk Average | Risk level |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| A | 2 | 4 | 1 | 4 | 2 | 2 | 2 | 4 | 1 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1.65 | Red |
| B | 0 | 4 | 1 | 4 | | 2 | 2 | 4 | 1 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1.04 | Red |
| C | 2 | 4 | 1 | 4 | 1 | 2 | 2 | 4 | 0 | 3 | 2 | 2 | 1 | 2 | 0 | 2 | 1.35 | Red |
| D | 2 | 4 | 2 | 4 | 2 | 2 | 2 | 4 | 1 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1.83 | Red |
| E | 0 | 4 | 0 | 4 | 1 | 2 | 2 | 4 | 0 | 3 | 2 | 2 | 1 | 2 | 0 | 2 | 0.57 | Green |
| F | 0 | 4 | 0 | 4 | 2 | 2 | 2 | 4 | 0 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 0.78 | Yellow |
| G | 2 | 4 | 2 | 4 | 2 | 2 | 2 | 4 | 1 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1.83 | Red |
| H | 2 | 4 | 2 | 4 | 0 | 2 | 2 | 4 | 1 | 3 | 2 | 2 | 0 | 2 | 2 | 2 | 1.61 | Red |
| I | 2 | 4 | 2 | 4 | 2 | 2 | 2 | 4 | 0 | 3 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1.70 | Red |
| J | 2 | 4 | 2 | 4 | 1 | 2 | 2 | 4 | 1 | 3 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1.74 | Red |
| K | 0 | 4 | 0 | 4 | 0 | 2 | 0 | 4 | 0 | 3 | 0 | 2 | 0 | 2 | 0 | 2 | 0.00 | Green |

ከላይ በተዘረዘረው ሂደት እና መስፈርት ድርጅቶች አጠቃላይ ኦዲት ከተመረጡ በኋላ የድርጅቶቹን የስጋት ትንታኔ በማካተት ለኦዲት የሚላክ ይሆናል።

## 2.6. ክትትልና ግምገማ /Monitor and Review/

አጠቃላይ አሰራሩን እና የመረጣ ሂደቱን ለመከታታል እና ለመገምገም መረጃዎችን አደራጅቶ ለስጋት ስራ አመራር የመላኩ ድርሻ ኦዲቱን ያከናወነው እና በዋ/መ/ቤት ደረጃ የኦዲት ስራውን የሚከታተለው አካል ይሆናል።

የክትትል እና ግምገማውን አስፈላጊት ስንመለከትም የመምረጫ መስፈርቶቹን ውጤታማነት ለመገምገም እና ለማሻሻል እንዲሁም ውጤታማነትን ለመመዘን ሲሆን በዚህም መሰረት ትክክለኛ እና ውጤታማ የስጋት ምዘና እና የስጋት መስተንግዶ መደረጉን ለመለካት እና ለማሻሻል ነው። የአጠቃላይ ኦዲት መረጣ ሂደቱ ውጤታማነት የሚለካው የስኬት መጠን/Success Rate/ እና

የሚካሄደው ለኦዲት ከተላለፉት ድርጅቶች የሚገኘን ግብረ መልስ መሰረት በማደረግ ይሆናል፡፡በዚህም መሰረት በክትትል እና ግምገማው ከታች የተዘረዘሩትን ጉዳዮች መልስ ለመስጠት እንችላለን፡-

- አዳዲስ ሊከሰቱ የሚችሉ ሥጋቶች/ የሥጋት አመላካቾች ምንድን ናቸው?
- የመስተንግዶ ስትራቴጂዎቹ ውጤታማነት እንዴት ነበር?
- ታሳቢ የተደረጉ ጉዳዮች ትክክል ነበሩ ወይ?
- የተሻለ ውጤታማ ለመሆን ምን ማድረግ አለብን ? እና የመሳሰሉትን በመመዘን የሚያስችል ይሆናል፡፡

የስኬት መጠን/Success Rate

የስኬት መጠን/Success Rate/ የሚሰራው በስጋት ትንታኔ መሠረት ቅደም ተከተል ወጥቶላቸው እንዲስተናገዱ ከተደረጉት ድርጅቶች መካከል በምን ያህሉ ላይ ውጤት እንደተገኘ በማስላት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ለመስክ ኦዲት ከፍተኛ የስጋት ፕሮፋይል ያላቸው ድርጅቶች ሆነው ኦዲት እንዲደረጉ ከተደረጉ 100 ድርጅቶች መካከል በምን ያህሉ ላይ ግኝት እንደተገኘ በማስላት የስጋት ስራ አመራር ማለትም ስጋት መምረጫ መስፈርቶች ትክክለኛነት ይገመገማል፡፡ ዝቅተኛ የስኬት መጠን/Success Rate/ በሚከሰትበት ጊዜ የመስክ ኦዲት የስጋት መረጣ ሂደት/PCA risk selection Process/ ላይ ጥያቄ የሚፈጥር ሲሆን የመምረጫ መስፈርቶች በመገምገም ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

የሕግ ተገዥነት መለኪያ/Compliance Measurement

ሌላው የስጋት መረጣው እና የኦዲት አሰራራችንን ውጤታማነት መለኪያ የሕግ ተገዥነት መለኪያን/Compliance Measurement/ በመጠቀም ነው፡፡ የሕግ ተገዥነት መለኪያ የስጋት ስራ አመራር ሂደት/Risk Management Process/ ውጤታማነት በተለይም የሕግ ተገዥነትን ከማምጣት አንጻር የታክስ ስጋቶችን ለመቅረፍ የተወሰዱ መስተንግዶዎችን ለመገምገም የሚያስችል መለኪያ ነው፡፡ የሕግ ተገዥነት መለኪያ የሕግ ተገዥነት መጠን /Compliance Rate/ የሚያሳይ ሲሆን ከተቀባይነት መጠን በታች የሆነ የሕግ ተገዥነት ደረጃ በሚፈጠርበት ወቅት ለሕግ ተገዥ እንዳይሆኑ የሚያደርጉ ምክንያቶች ወይም ባህሪያት ይጠናሉ፡፡ በጥናቱ መሰረት ለእያንዳንዱ ባህሪ ተመጣጣኝ የሆነ የመስተንግዶ ስትራቴጂዎችን በመንደፍ ሊተገበር ይችላል፡፡

በመሆኑም በሚደረጉ ክትትል እና ግምገማዎች መሰረት የስጋት መምረጫ መስፈርቶች እና አጠቃላይ የአሰራር ማኑዋሉ በየጊዜው ሊሻሻል ይችላል፡፡

## ማጠቃለያ

በአጠቃላይ የአጠቃላይ ኦዲት መረጣ ስራው ከላይ በተቀመጠው አሰራር መሰረት የሚከናወን ሲሆን ለኦዲት መረጣው በስጋት መመረጫ መስፈርቶች ትንታኔ መሰረት የሚከናወን እንደ መነሻ በመውሰድ መስፈርቱ ይረዳሉ ተብለው ከላይ በዝርዝር የተቀመጡትን መረጃዎች በቅደም ተከተል መሠረት የሚተገበረው በኦዲት ሽፋን ግዜ ውስጥ ያሉትን ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት በማደራጀት በሚገኙ ውጤቶች ላይ በመመስረት የሚከናወን በየጊዜው እያሻሻሉ ለመሄድ እንደ የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ስራን በስጋት የመምረጥ ቀርቧል፡፡ ይህንም መነሻ በማስፋት መነሻ ይህ ሰነድ ተዘጋጅቶ የአሰራር ማኑዋል ሆኖ የመረጣ ስራውን የማከናወን በቀጣይ አሰራሩን በማስፋት እና በማዘመን በሲስተም ከተዘረዘሩት ውጪ የሆኑ አሰራር ተግባራዊ ሲሆን ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከላይ የበለጠ አጋዥ የሆነ ለኦዲት መረጣው የሚያግዙ መስፈርቶችን በማካተት ለስራው አሠራር ሥርዓት መዘርጋት እንደሚቻል ለማሳየት መነሻ ይሆናል፡፡